# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

የካቲት 16 ቀን 2003 ዓ.ም.

## የኢሕአፓ ቀስቃሽ መልዕክቶችን ያዘሉ በራሪዎች መሰራጨት ቀጠሉ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ወሳኝ ትግል በወያኔ አናት ላይ እንዲፈነዳ እየተደረገ ያለውን ሁለገብ ጥረት በተጨባጭ ለማገዝ የኢሕአፓ ቀስቃሽ መልአክቶችን ያዘሉ በራሪዎችና ተለጣፊ ወረቀቶች በአዲስ አበባ አስሩም ክፍለ ከተሞች ባለፈው ቅዳሜ የካቲት 12 ተሰራጭተዋል፣ ተለጥፈዋል።

ከዚህ በፊት እንደታየው ሁሉ በአሁኑ ወቅትም በራሪ ወረቀቶችን የማሰራጨትና የልጠፋው ተግባር አለ ምንም እክል ሊጠናቀቅ መቻሉ የተገለፀ ሲሆን ብርክ የያዘው ወያኔ በፀጥታ መስሪያ ቤቱ የኢሕአፓ መምሪያ መኮንኖችንና የፀጥታው ክፍል ሀላፊዎችን ዳግም ለልዩ ሰብሰባ ጠርቶ ንዴቱን መግለፁም ሊታወቅ ተችሏል። ኢሕአፓ በቀጣይ መልክ በዚህ አንቅስቃሴ የተሰማራውና አስፋፍቶም ሊያካሂደው የተነሳው አንድም የወያኔ ግዙፍ የፀጥታ መዋቅር ተሸናፊ መሆኑን ለማሳየት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝብን ለትግል ለመጥራት ነው። የአብዮት ነፋስ አህጉራችንንና መካከለኛ ምሥራቅን እያመሰ ባለበት በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያም የለውጥ ምድር መሆን እንድትችል ድርጅቱ አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ይገልጻል።

በስልትና በትብብር ለወሳኙ ፍልሚያ እንዘጋጅ!

ሕዝብ በመለስ አገዛዝ ላይ ድልን ይቀዳጃል!!!






